## መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
### አቅራቢዎች



# ከወንዙ የመጣው ልዑል


ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): M. Maillot; Sarah S; Alastair Paterson
የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada



©2021 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዮሴፍ ሞተ! ሁሉም የግብፅ ሰዎች የቤተሰቡን ሀዘን ይጋሩ ነበር። እግዚአብሔር አገሪቱን ከረሃብ ለማዳን በእብራዊው ዮሴፍ



ተጠቅሞበታል። እርሱ ጥበበኛና የተወደደ መሪ ነበር። አሁን ግን ሄዷል።

ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ አለፈ። የዮሴፍ ሰዎች, ዕብራውያን በግብፅ ውስጥ ታላቅ ዘር ሆነው ነበር። አዲሱ ፈርዖን ዕብራውያን በእርሱ ላይ ሊነሱበት እንደሚችሉ ፈርቶ ስለነበር ሁሉንም ባሪያዎች አደረጋቸው።




ፈርዖንም ዕብራውያንን በጭካኔ ይገዛቸው ነበር። ታላላቅ ከተማዎችንም እንዲገነቡ አስገደዳቸው። ነገር ግን ምንም ያህል ከባድ ቢሆንም የዕብራይስጥ ባሮች ቁጥራቸው እየጨመረ ሄደ።




አንድ ቀን, እጅግ አስፈሪ ትዕዛዝ ከፈርዖን ዘንድ መጣ። ይህም "አዲስ የተወለዱት ዕብራውያን ወንዶች ሁሉ ወደ ናይል ወንዝ እንዲጣሉ" የሚል ነበር። ክፉው ፈርዖን የዕብራውያንን ቁጥር ለመቀነስ ቆርጦ ነበር።




"ምን እናድርግ?" አንድ ቤተሰብ ተጨነቁ። በኋላ ግን አንድ ውሳኔ ላይ ደረሱ። እሱም ህፃኑን በቅርጫት ውስጥ ከተው በናይል ወንዝ ዳር ማስቀመጥ ነበር።




እጅግ ውብ የሆነው ጭነት ከመርከቡ ላይ ተንሳፈፈ። ትንሹ ሕፃን ላይ ምን ይፈጠር ይሆን?




የሕፃኑ እህት በባህሩ ላይ ያለውን ውቡን ቅርጫት ከሩቅ ትመለከት ነበር።




በድንገት ግን የፈርዖን ሴት ልጅና አገልጋዮቿ ለመታጠብ ወደ ወንዙ መጡ። ቅርጫቱ ከአይናቸው የሚደብቅበት መንገድ የለም ነበር። ምናልባትም ይህን ሳያዩ በእግራቸው ይራመዱ ይሆናል።
9
የፈርኦንም ልጅ "ኦ ቅርጫት, ተመልከቱ በቀጤማው ላይ" በውስጡ ያለው ምን እንደሆነ ለማየት ቸኩያለሁ "ብላ አገልጋዮቿ ን ሄደው ቅርጫቱን እንዲያመጡ አዘዘቻቸው። ቅርጫቱም ሲከፈት - ሕፃኑ ማልቀስ ጀመረ። ንግሥቲቱ" ይህ ዕብራውያን ልጅ ነው" ብላ ተደነቀች።
10
የፈርኦን ልጅ ህፃኑን "አንተ ትንሽዬ በጣም ቆንጆ ነህ" እያለች ብዙ ትላልቅ ሰዎች እንደሚያደርጉት ታዋራው ነበር። እንዲያውም በግብፅ ቋንቋ..."ኦቶቼኪ-ኩኪኪ ኬኦ-ሹም" እያለች ታጫውተው ነበር።
11
እግዚአብሔር ለህፃኑ እህት ልዩ ጥበብን ሰጣት። ወደ ፈርዖን ሴት ልጅ ሮጣ ሄዳ "ህፃኑን ለመንከባከብ ከዕብራውያን ሴት ልፈልግልሽ" አለቻት። "ሂጂ ፈልጊ" ብላ መለሰችላት። ልጃገረዷ ማንን ለማምጣት የሄደች ይመስላችኋል?
12
"እናቴ ፈጥነሽ ነይ እባክሽ ፍጠኚ" ብላ አጣደፈቻት። ምናልባት ይህች ልጅ ለእናቷ ለመናገር ጊዜ አልነበራትም። ሁለቱም አንድ ላይ ሆነው ወደ ቦታው ተጓዙ።
13
ወደ ወንዙ ሲደርሱ የፈርዖን ሴት ልጅ ህፃኑን አቅፋው ነበር። ለእናቱም "እባክሽ ተንከባከቢው ለዚህ ደግሞ እከፍልሻለሁ ስሙንም ሙሴ ብዬዋለሁ" አለቻት። ሙሴምናልባት ግብፃዊው የውሃ ልጅ ሊሆን ይችላል።
14

ስለዚህ ሙሴ ወደ ቤተሰቦቹ ተመለሰ። እነርሱም እግዚአብሔርን እና የዕብራይስጥን ህዝቦች እንዲወድድ ያስተምሩት ነበር። ብዙም ሳይቆይ ከፈርዖን ሴት ልጅ ጋር ቤተ መንግሥት ውስጥ መኖር ጀመረ። ህይወቱን ያተረፈው እግዚአብሔርም ለህፃኑ ሙሴ ታላቅ የወደፊት ዕቅድ ነበረው።





**ከወንዙ የመጣው ልዑል**

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

**ዘፀዓት 2**

"የቃልህ ፍቺ ያበራል."
መዝሙረ ዳዊት 119:130



# መጨረሻ

9 60



ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር "ኃጢአት" ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16